ትንሸ ስለአዲሳበባው ተውኔት

Oct 19 at 7:01 PM

## የወያኔ  የአዲስ አበባ የስብሰባ አዳራሽ “ድራማ”

ከሁሉም የልደቱ አያሌው የእራቁትነት ገመና ገረመኝም አሳቀኝም። ምንድን ነው የሚያስቅ የሚለኝ አይጠፋም ለእኔ ሰሞኑን ብዙ ወገኖች ይህን ሰው ስም እዚህ በማህበራዊ ድህረገጽ ሊኖረው የማይገባ ክብር ሊሰጡት የዳዳቸው አየሁ። አልፈርድም። ምክንያቱም አረዳዳችን የተለያየ ነው እና የተለያዩ ሰወች በተለያየ ነገርን አዳምጠው ይተረጉማል። እናም ልደቱ ከ 11 አመታት በኋላ ብቅ ብሎ በዚህ መድረክ ከተናገራቸው ምንም እንኳን አዲስ ባይሆንም አቋሙን የበለጠ አጠናክሮ የሕወሐት አንድ አባል ሆኖ መቅረቡ ነው።

ድንቁም ማንዴላ ሆነች ልደቱ ዛሬ ሕወሐት አሁንም የለውጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ይገባል ብሎን አረፈ። ሁለት እድል ነበረው ኢንጅነር ይልቃል እና ዶክተር መረራ ያቀረቡትን ሀሳብ ልጅ እንደመሆኑ መጠን ቢያዳምጥ ኖሮ የማያስገምት ሀሳብ ሊያቀርብ በቻለ። ያም ባለመሆኑ መቸም በዚህች አገር ነገር ከዳር አይደርስም ልደቱም ዳግም የከሸፈ ተቃዋሚነቱን ለቀቅ አርጎ በሕወሐት አባልነት ቢቀጥል ያምርበታል ማለት ነው። ሌላው ማን ነው ማሞ በሚል የአያት ስም የያዘ ጋዜጠኛ መሆኑ ነው።

አህያውን ፈርተው ዳውላውን ይባላል። የስርአቱ ቱባ ፋሽስቶች እዚያ ቁጭ ብለው ታዛዥ ጓደኞቹን (ባንዳን) ሊወቅስ ተነሳ። መቸም የማፈሪያ ግዜ እና አገር ነን በረከት ስመኦን ቢሮ ገብቶ ተሳድቦ እንደሚወጣ አውግቶ ተቀመጠ። ምን ማለት ነው? ዴሞክራሲ አለ ሊለን ነው ይሆን?

በ 1930 ወቹ ኢትዮጵያ በቢኒቶ ሞሶሎኒ ስትወረር እና ይህች አገር የሊጉ አባል መሆኗ እየታወቀ እና የቨርሳይ ስምምነትን እንደፈረመች ሁሉ የአባል አገራት ወረራውን መጋራት ሲኖርባቸው በግዜው ሂትለርን በመፍራት መጀመሪያ በእኛ አገር ኋላም በቸኮዝሎቫኪያ፣ ሆላንድ እና ግሪክ ተመሳሳይ ፖሊሲ ተከተሉ።

ለዚህ ፖሊሲ ደግሞ appeasement የሚሉት የአንግሎ-ፍራንኮ ስምምነት የውጭ ፖሊሲ ይባል የነበረውን መስመር በመያዝ ሲሆን። ይህ ፖሊሲ ከሂትለር ይልቅ እስታሊን ያስፈራናል ከሚል እምነትም የተቆራኘ የማደናቆር (ማለሳለስ) ፖሊሲ ነበር።፡የኋላ ኋላ ፈረንሳይም እንግሊዝም ከሂትለር ዱላ አላመለጡም እንዴውም የፈረንሳዩ ላቫል የሂትለር ባንዳ እስከመሆን እንደደረሰ ታሪክ ይሳለቃበታል።

ይህ የወያኔ ስብሰባ አስመሳይ እና ልክ እንደየያኔው የአንግሎ-ፍራንኮ ፖሊሲ appeasement መሆኑ ነው። ዶክተር ፈቃዱ በቀለ በሰሞኑ ያቀረቡልን ግሩም መጣጥፍ አለ እናም “ወያኔ ሊታደስም ሊታከምም የሚችል ሀይል አይደለም! መወገድ ያለበት እንጅ!” ይላል እረእሱ። በጣም እስማማለሁ። ሕወሐት የከሰረ ዘረኛ ድርጅት ናት።

ከሁሉም በላይ ከህዝብ ጋር ሊያስታርቃት የምትችለውን የግዜ ገደብ ተላልፋለች። የግዜ ገደቡ የኢትዮጵያውያን ደም ነው። ለአቶ ልደቱ ይህ የሚገባቸው አይደለም። ሀይሌ ገብረስላሴ እንኳን በቃችሁ አልቋል ሲል ሰማሁ።

ወያኔ በጎን የጎንደርን፣ የጎጃምን ሕዝብ፣ በቋሚነት ጠላቴ የምትለውን አማራውን ዛሬ በዚህች ሰአት እየገደለች አዲስ አበባ በተዋበ ሰፊ አዳራሽ ትቂት የተቃዋሚ ልሳን ጨምራ ትያትር አሳየችን። በኦሮሚያ በአንድ ጀንበር 1000 ዜጎች ያም 50000 በሚኖርበት መንደር ሰብስባ እስር ቤት ከተተች። ይህ አህዝ 20% የሚሆኑትን ነዋሪወች አሰረች።

ይህ መነገር አለበት፡ በየአደባባዩ ሁሉም እንዲያውቅ መሆን ይኖርበታል፡ ምክንያቱም አዲስ ያለተለመደ የጠላት ስራ ስለሆነ። እናም ከእንደዚህ አይነት መንግስት የተሻለ መጠበቅ እጅግ የዋህነት አለያም ማደናቆር ይመስለኛል። በፋና ብሮድካስቲንግ ተቀነባበሮ የቀረበ ድራማ ልክ ከላይ እንዳልሁት ነገርን የማዳፈን ጅማሮ መሆኑን ሁሉም ዜጋ እንዲያውቀው ይሁን።

ለምሳሌ ልደቱ በተቃዋሚ ስም ተቃዋሚውን በይበልጥም ተገፍቶ አገር የተነፈገውን “ጽንፈኛ” የሚል ባንዳ ነው። አሁንም ባንዳ ነው። አወ እየመረራቸውም ይልቃልን እና መረራን ጨምረዋል። ሌሎችም ትቂት ልሳኖች ሰምቻለሁ። ሆኖም እነዚሁም ቢሆን እውነቱን ነው የነገሯቸው። ግዜው አልቋል በቃ ነው ያሉት።

ሕወሐት ግን ያው ተወልዳ ያደገችበትን ድራማ በጎን በአስር ሽሆች ወደ እስር እየወሰደች እና እያጎረች። በታች አርማጭሆ፣ በጸገዴ፣ በመላ ጎንደር እና በመላ ጎጃም፤ በሁሉም የኦሮሚያ ቀበሌወች መደበኛ የጦር ሰራዊት ከአጋዚ ፈጥኖ ደራሽ ጋር አሰልፋ እየገደለች አዲስ አበባ ይህን ድራማ ሰርታ ይኸው እኛም ለማየት በቃን። የጉድ አገር ናት እና ሁል ግዜ ጉድ እናያለን።

በዚህ ጉዳይ ይህን የሕወሐት የማጥቃት ግንባር ትንታግ የሆኑ ወጣት ምሁራን ስለአሉ በመልካም ይከውኑታል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ። እንደቻልን እንመላለስበታለን። ግን ዶክተር ፈቃዱ በቀለ እንዳሉት “ሕወሐት የምትታከም ሳይሆን መወገድ ያለባት ነቀርሳ ድርጅት ናት”።

ግዜው ሕወሐትን አስወግዶ ሁሉም ዜጎች በሰላም፣ በዴሞክራሲ እና በፍቅር የሚኖሩባት አገርን ማስመለስ ነው። ትግሉም ሕወሐት ትታደስ አይደለም። ሕወሐት ወንጀለኛ ድርጅት ናት። የሕወሐት አመራር አባላት በደም የተጨማለቁ ወንጀለኞች ናቸው። የእነርሱ ቦታ ለወንጀለኛ የሚገባው ቦታ እንጅ አገር ማስተዳደር ዳግመኛ አይሞከርም። ወንጀለኛ ተናዞ እና ንስሀ ገብቶም እንኳን ወደቦታህ ተመለስ ሊባል አይገባውም።

ለወንጀሉ ምክንያት ወንበሩ በመሆኑ ቦታው ስላልሆነ ማለት ነው። ሕወሐትን ማስወገድ እንጅ ማደስን ወጊዱ ብሏል። ይህ ደግሞ በነቂስ የኢትዮጵያ ሕዝብ እየሞተም ወጥቶ በመትረጌስ ፊት ቆሞ ሕወሐት ትወገድ ነው ያለው። በኤሬቻው ባእል ላይ ትንታጉ ሞት አይፈሬ ወጣት ወጥቶ Down! Down! Down! እስከወዲያኛው በመልካሟ ኢትዮጵያ የታሪክ ማህደር ይኖራል።

እኛም ሕወሐት ትወገድ ዘንድ እንተባበራለን

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ግዜ የማይሽረው ከዚያ ትውልድ አንድ ግጥም

http://yatewlid.com/mp3/Tegil_Minun_Tegil_Hone.mp3

መንግስቱ ሙሴ

<mmusie2@gmail.com>

http://www.ethiopanorama.com